# ሥልጡኑ ጎረቤቴ እና እኔ

ከበልጅግ አሊ

-፩-

ጎረቤቴን በጣም እወድዋለሁ፣እሱም ይወደኛል ። ለብዙ ዓመታት አብረን ጎን ለጎን ኖረናል ። እንመካከራለን ፣ እንወያያለን ፣ችግር፣ ሃዘን፣ ደስታም አብረን እንካፈላለን ።ገና ወንደላጤ ከነበርንበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ትዳር ይዘን ልጆች ወልደን እስከምናሳድግበት ድረስ ጎረቤታሞች ነን።ልጆቻችንም አብረው ነው የሚጫወቱት ።የዓመት በዓልም እንደ ሃገራችን ደንብ አብረን ነው የምናሳልፋው ።

ጎረቤቴ ያለውን ሁሉ ለኔ ከማካፈል ወደ ኋላ አይልም ። እንደው ሞቅ ያለ ምግብ ከተሠራ እንኳ ካለኔ መብላት ይቀፈዋል ። እኔም ለሱ ወደ ኋላ አልልም ። በተቻለኝ መጠን የጠየቀኝን ለማድረግ እጥራለሁ። ብዙ ዓመታት በጉርብትና ስንኖር የከረረ ለጠብ የሚያደርሰን ነገር አላጋጠመንም ።

የሥራ ክፍፍል ሳናውቀው አድርገናል ። ጎረቤቴ የምንኖርበትን ሃገር ቋንቋ ለመማር ፍላጎትና አቅም ስለሌለው የሃገሪቱን ዜጎች በዘረኝነት ፣ቋንቋቸውን በተባባሪነት እየወነጀለ ቋንቋውን ለመማር ጥረት አያደርግም ። ቢሆንም አንዳንድ የቋንቋውን ቃላትም አማርኛው ውስጥ በመደባለቅ በአካባቢው እንደ አዋቂ ይቆጠር እንጂ ከመንግሥት የሚመጡ ደብዳቤዎችን የማንበብና የመመለስ ፣ ፎርሞች የመሙላት ፣ ስልኮችን የመደወልና አንዳንድ የዚህ ሃገር ቋንቋን የሚጠይቁ ጉዳዮችን ማስፈፀም ለኔ ተመድቦልኛል ። ጎረቤቴ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ተጠሪያችን ነው ። እኛን ወክሎ አዳዲስ ሁኔታዎች ማጥናት፣ ለእኛ እያመጣ በሰፊው ማስረዳት፣ መወሰን፣ እሱ ልክ ብሎ ያመነበትን እንድንቀበል በቁጣ ፣ በማኩረፍና ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማሳመን ለእሱ በፈቃደኝነት የወሰደው ሥልጣኑ ነው። በአካባቢው ስለሚፈፀሙ ሁኔታዎች ጠንቅቆና ከሰው ቀድሞ ስለሚያውቅ ፣ ስለ ታመመ ሰው ፣ የተረዳ ጎረቤት ፣ ሰላም ያጣ ትዳር በሞላ እንድናውቅ ያደርገናል።

ታዲያ ጎረቤቴ አንድ ችግር አለበት ።ችኩል ነው ። ለማመስገንም ፣ ለመቃወምም ፣ ለመጣላትም ፣ ለመፋቀርም ይቸኩላል ። ዛሬ የተናገረውን የዛሬ ሁለት ወር ይረሳዋል ። ዛሬ የሆነውን ነገ መሆን አይፈልግም ። የወቅቱ የአኗኗር ዘዴ በጣም የገባኝ ነኝ ባይ ነው ። እኔም አምንለታለሁ ገብቶታል ።በዚህ ጥድፊያ በበዛበት ዓለም ውስጥ ለመኖር እንዲህ መሆን ያስፈልጋል ብሎ ማመን ብቻ ሳየሆን ተለዋዋጭነትን በተግባር ተርጉሞ እየኖረበት ይገኛል ።

በአንድ ወቅት ለሁለት ሳምንታት ከአጠገቤ ጠፋና እኔ የዋሁ ደግሞ በትዳሩ ውስጥ ችግር አጋጥሞት ይሆን ? እያልኩ ሳወጣ ሳወርድ ከረምኩ ። ቢቸግረኝ ደውዬ፣ እንድንገናኝ ፈልጌ የራሱን አባባል በመጠቀም "ምጣ" አልኩት ።እንደልማዱ ሰሞኑን ከኛ ነጥሎት የነበረውንና ይጠቅማል ብሎ ያሰበውን አዲሱን ግኝቱን ይዞ ብቅ አለ።እንደው ደህንነቱንና ምን ሆኖ እንደጠፋ መጠያየቅ ስጀምር ምንም ግዜ ሳይወስድ፡ -

"ሁላችንም ኢየሱስን መቀበል አለብን" አለኝ በችኮላ ።

"እስከ አሁን አልተቀበልንም እንዴ?"አልኩት በፈገግታ ምን ማለቱ እንደሆነ እንዳልገባው።

"ቢሆንም ቸርች መሄድ አለብን።" ጥያቄዬን ችላ በማለት።

"የትኛው ቤተክርስትያን ?" አልኩት "ቸርች" ማለቱ ለምን እንደሆነ እንዳልገባኝ በማስመሰል።

ቦታውን ሲነግረኝና የትኛው "ቸርች" መሆኑን ሳውቅ ሰሞኑን ምን እንዳጠፋው ለማወቅ ብዙም ጊዜ አልወሰደብኝም ። እሱም ሳይደብቀኝ ኢየሱስን መቀበሉን አስረዳኝ ። ጉርብትና የጋራ፣ ሃይማኖት የግል መሆኑን አስረድቼው ሃይማኖቱን መጋራቱን ትተን

ጉርብትናችንን ቀጠልን ። የተለወጠ ነገር ቢኖር ጨዋታችን ነበር ። እሱ መካሪ እኔ ተመካሪ ፣ እሱ ፃድቅ እኔ ሃጢያተኛ ፣ እሱ ድምፅ ያለው ዘማሪ እኔ ደግሞ ሰሚ ፣ እሱ አንገቱን የደፋ፣ ልቡ የተሰበረ ፣ እኔ ደግሞ ገና ያልተለወጥኩ "የዓለም ሰው" ነን ብሎ ማሰቡ ብቻ ነበር ። ሌላው በኋላ ቆይቼ ያየሁት ቤቱ ውስጥ ለወትሮው ተሰቅሎ የነበረውን የማርያም ስዕል ከቦታው ማንሳቱ ነው ። ይህንን ያየሁ ግዜ ምንም አልተናገርኩ።ልጅን ወዶ ከእናት ጋር ጠብ ብዬ ለብቻዬ አልጎመጎምኩ።

በዚያ ወራት ጎረቤቴ መጽሐፍ ቅዱስ የማይለየው ፣ ለአገኘው ሁሉ ስለ ኢየሱስ መስካሪ ሆኖ ፖለቲካን ደግሞ እርግፍ አድርጎ ትቶ ነበር ። ለነገሩ ድሮም ቢሆን ፖለቲካው የሞቀበት ሁሉ እየተጣደ በማያውቀው እየተከራከረ ተቸግረን ነበር ። ለወሬ ነጋሪ በቅርብ ግዜ በተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች ያልገባበት የለም። በየወቅቱ እየሞቁ በሚጠፉ ድርጅቶች ሁሉ ሲሆን በፈቃደኝነት ተመራጭ ሳይሆን አባል እየሆነ ከድርጅት ወደ ድርጅት ሲሸጋገር ምንም አይመስለውም ።በፖለቲካ ምክንያትስ የሚጣላው ብዛቱ ! እንዲያውም ጎረቤቴ ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ ምረጥ ብባል የአሁኑ ሃይማኖተኝነቱ ይሻለኛል።እንደ ፋሽን ካፖርት ድንገት የደረበውን "ኢየሱስን" አልቀበልም ማለቴ የዘመኑ ፍፃሜ መድረስ አመልካች መሆኑን በሀዘኔታ እየተናገረ እኔን ጎረቤቱን ለማዳን በአዲሶቹ ወንድሞቹ አማካኝነት ፀሎት እንደሚያደርግልኝ ይነግረኝ ስለነበር ጉዳቱ አይታየኝም ። ይልቁንስ እኔን ያሰለቸኝ የነበረው ከየከተማው ሰብስቦ የሚያመጣውን ፖለቲካ አይሉት ቅራቅንቦ ወሬ ስህተቱን ከደህናው አጣርቼ ለማስረዳት የማደርገው ጥረትና የእሱ ልብ አውላቂነት ነው።

ሃይማኖቱን ከቀየረ በኋላ ይህንን ሁሉ የፖለቲካ ሕይወቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ ሰላም ወርዶ እያለ አንድ ቀን በድንገት የከረረ ክርክር ውስጥ ገባን ። የወያኔን መንግሥት በተለይ መለስን ኢየሱስ ስለሾመው እኛ በዘረኝነትን አሳበን "ጌታ" የሾመውን ሰው ከሥልጣን ለማውረድ መታገል የለብንም አለኝ ። እኔ ደግሞ መለስን የሾመ ኢየሱስ ሳይሆን ሰይጣን ነው ። ይህንን በሃይማኖቱ የፀናን ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት እንዲከፋፈል የሚጥር ሰይጣን ነው እንጂ ኢየሱስ አይደለም ። ይህንን የወያኔን እኩይ ተግባር እንድንዋጋ ፣ ፍቅር ፣አንድነት እንዲወርድ እንድንታገል ፣ እኛም ዘረኝነትን ፣አድሎን እንድንቃወም የፈቀደልንና ስለፍቅር ያስተማረን ኢየሱስ ነው አልኩት ።

በዛ ሰሞን አንድ ፓስተር ከአዲስ አበባ መጥቶ የተማረው የግዜው አንገብጋቢ ጉዳይ የመለስ ሥልጣን ስለነበር የኔን ሃሳብ ተዘባነነበት፣ እኔንም እንደ ኃጢአተኛ ቆጠረኝ እንጂ ሊቀበለው አልቻለም ። እኔም የጎረቤቴን ተለዋዋጭ ፀባይ በማወቅና በቅርብ ደግሞ እንደሚቀየርና ሌላ አዲስ ሃሳብ እንደሚያመጣ እርግጠኛ ስለሆንኩ ለማሳመን ብዙም አልደከምኩም። ብለፋም ብጥርም ወቅታዊነቱ (ፋሽኑ) አልፎ በሌላ እስከሚተካ ጓደኛዬን ለማሳመን መጣር ጥቅም እንደሌለው አውቀዋለሁ ። ሁለታችንም የየራሳችንን ጠንካራ አቋም ይዘን መከባበርን መርጠን በዝምታ ተለያየን።

ከዚህ ሁሉ ግርግር በኋላ አንድ ቀን ወደ ቤቴ ብቅ ብሎ አዲስ አበባ ለመሄድ እንደወሰነና ለቤተሰቤ የምልከው ደብዳቤ ካለ እንዳዘጋጅ ነገረኝ ። ድሮ ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት ይነግረኝ ነበር። እኔም በውሳኔው ሳልከፋ ጥሩ ውሳኔ መሆኑንና መልካም ምኞቴን ገልጬለት ወደ ሃገር ቤት ጉዞ አደረገ።

ከአዲስ አበባ ሲመለስ በኃይማኖቱ ፀንቶ ፣ በዚያች ሃገር ያለውን መከራና ችግር ተመልክቶ ፣ የተሻለ ዘመን እንዲመጣ ፀሎቱን አድርሶ ይመጣል ብዬ ስጠብቅ ፣ ጎረቤቴ ባልጠበቅሁት ሁኔታ አዲስና ልዩ በሆነ መልክ ተለውጦ ብቅ አለ ።

ይዞት የመጣውን ምግብ ልንበላ ተሰብስበን ሳለ ያንን ረጅም ፀሎቱን ሲዘነጋው መለወጡ ግልፅ ብሎ ታየኝ ። እዛ የተሰበሰብነው በሁኔታው ተደናግጠን እንደምንም አስታውሰነውና አጠር ያለችና የግል አሰተያየት ያልተጨመረባት የማታሰለች ፀሎት አድርጎ አስደነቀን ። ያ ድሮ የአዋቂነቱ ምልክት አድርጎ የሚጠቀምበት፣የተንዛዛው ንግግር

እንደመፈክር ባነሰች በመተካቱ ቶሎ እኛም ሃሳቡን እንዳይቀይር በመፍራት በተራችን "ሥላሴዎች ማዕዱን ይባርኩት" ብለን ከሃገር ቤት የመጣውን ምግብ ተቋደስን ።

ከአዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ አንድ ቀን ወደ ቤቴ ብቅ አለ ።ያ አንድ ሰሞን ከእጁ የማይጠፋው መጽሐፍ ቅዱሱ የለም ። ጨዋታ ተጀመረና ስለ አዲስ አበባ ጠየቅሁት ። በተዝናና ሁኔታ ፎቴው ላይ ከተስተካከለ በኋላ ፡ -

"አዲስ አበባ በጣም ሠልጥናለች ። የሕዝቡም ኑሮ ተቀይሯል ። ደሃ የሚባል ከተማው ውስጥ አይታይም ። ሁሉም አየር ባየር መነገድ ነው ። ገንዘብ በገንዘብ ነው ። እኛ ግን እዚህ ፖለቲካና ዘላለም ለማያልፍላት ሃገር "ሃገር ፣ ሃገር " ስንል በጣም ተጎድተናል ። አሁን ግን ለራሳችን ማወቅ ይኖርብናል ። ሃገሪቷን ማንም ይግዛት ማንም፣ ምንም ትሁን ምን፣ ኑሯችንን መቀጠል ነው ያለብን ። ስታስበው ዞሮ ዞሮ ራስን ማዳን ማለት ሃገርን ማዳን ነው ።የማንም ፋራ ባላገር እየመጣ ኢንቨስተር በሆነበት ሃገር እኛ የአራዳ ልጆች ውሃ ሊበላን አይገባም ። ወያኔ አያሰራም የሚባለውን አትስማ ። ሃገሪቷ ትሪያንግል ውስጥ ነው ያለችው ። ከላይ ትንሽ ሰዎች አሉ ። እነርሱ ትግሬ ሊሆኑ ይችላሉ ። እነርሱ ጋር ለመድረስ ከተመኘህ ስለምትጠፋ እሱን እርግፍ አድርገህ መርሳት አለብህ ። ከመሃል ትንሽ ቁጥራቸው የሚበዛ ሰዎች አሉ ። እሱ ጋር መግባት ትችላለህ ። የትሪያንግሉ ግርጌ ብዙ ሰው ነው ያለበት ። እሱን መመልከት የለብህም ። እነሱም ቢሆኑ የሚበሉት አያጡም ።.........."ብሎ አዲስ ሰበካውን ቀጠለ።

ጎረቤቴ ባለፈው ተቀበልኩት እያለ አዋጅ የነገረበትን "ኢየሱስ" አዲስ አበባ ለድሃዎች ሰጥቶ እሱ የዲታነት/ የኢንቨስትመንት ራዕይ ይዞ እንደመጣ ገባኝ ።ስለ ሃይማኖት ወሬም የለም ። እኔም የሆዴን ትዝብት በሆዴ ይዤ ወሬው እንዳይቋረጥ ያህል ምን መስራት እንደሚያስብና ግቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው እንዴት እንደሆነ ጠየቅሁት ።

"አንተ ከዚህ በኢንተርኔት ከአውሮፓ ሃገሮች መኪና እየገዛህ ወደ አዲስ አበባ ትልካለህ ። እኔ አዲስ አበባ እየተቀበልኩ እሸጣለሁ ። አንተ ከዚህ ገንዘብ የሚልክ ሰው እያፈላለክ ገንዘቡን ትቀበላለህ። እኔ እዚያ በብር እሰጣለሁ ።በገንዘቡ መኪና ገዝተህ ትልክልኛለህ"አለኝ ።

የውጩን ሃገር የንግድ ሥራ እኔ እንድሰራ አስቦበት እንደመጣ ገባኝና "ሃሳብህ ጥሩ ነው።እኔ ግን ለንግድ ሥራ አልስማማምና ለምን ሌላ አትፈልግም?"ብዬ ጠየቅሁት ።

"ድሮም እንዲህ እንደምትለኝ ገብቶኛል ። ግን አንተ ሁል ጊዜ እናት ሃገራችን ስትል ሌሎች ተቃዋሚዎች የት እንደደረሱ ልንገርህ እንዴ ? በአዲሱ ፖለቲካ ንግድና ትግል አይገናኙም ። ከመንግሥት ጋር መነገድ ትችላለህ ፣ መታገልም ትችላለህ ። እነማን እንደዚህ እንደሚያደርጉ ልንገርህ ? ብሎ የለበጣና የማሽሟጠጥ ፈገግታውን አሳየኝ ።የዘመኑን ፖለቲከኛ ነን ባዮች ታሪክ በሚመለከት እኔም የሰማሁትን ስለማውቅ እነማንን ሊጠቅስ እንደፈለገ ገብቶኛል።በዛ መቀጠል እንደማያወጣኝ አውቄ ፣ተቻናፊነቴን ተቀበልኩና ወደ ሌላው ጥያቄ ተጓዝኩ ።

"ለመሆኑ ድህነት ጠፍቷል ነው እንዴ የምትለኝ አልኩት ?"

ፈገግ ብሎ ድህነት በሱ ዝብርቅርቁ በወጣ አዕምሮ ላይ ተፈጥሮ በእሱው ዓይን ላይ የሚጠፋ ይመስል። "ድህነት እኮ ያለው ላየው ነው ላላየውማ የትም የለም ደግሞ ደሃን ከፈለግህ እዚህ ሠለጠነ የተባለው ሃገርም ውስጥ አለ ። ለማንኛውም አሁን ቀጠሮ አለኝ፣ ሰዎች ይጠብቁኛል፣ ሌላ ጊዜ በዚህ ጉዳይ እንነጋገራለን" ብሎኝ ጥሎኝ ሄደ ። ችኮላው አዲስ ጓደኞች ፣ አዲስ ፍቅር እንደጀመረና ከእኔ ጋር ጊዜ ለማጥፋት ፍላጎቱ እንደሌለው ያሳብቃል። ከሁኔታው ሁለተኛ እንደማይመለስና ይህንን አጀንዳ እንደማያነሳ ገብቶኛል ።

ከዛ በኋላ ከጎረቤቴ ጋር ስለ ሃገራችን የተነጋገርነው በቅርብ ነው ። የጎረቤቴ ሕይወት ተለውጦል ። የልጆቹን እናት ፈትቶ አዲስ አበባ አዲስ ሚስት አጭቷል ። ቤት ሠርቶ ጨርሷል ። የኢትዮጵያ ኤንባሲ ውስጥ ጉዳይ ላላቸው ሰዎች አስተርጓሚ፣አማካሪ፣ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኗል ። እዚህ ከሚኖርበት ጊዜ የበለጠ አዲስ አበባ ነው የሚኖረው።በንግግሩ ጣልቃ የወያኔ ባለሥልጣናት ስም አይጠፋም ። የባለሥልጣኖችን ስም ሲያቆላምጥ ለተመለከተው የቅርብ ግንኙነት አለው ብሎ መጠርጠሩ አይቀረም ። ግን ድሮም የገባባቸውን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ቢያውቃቸውም ባያውቃቸውም ደርሶ ሲያቆላምጥ ስለማውቀው ልማዱ መሆኑ ገብቶኝ አልደነቀኝም ። ግን ከገንዘብ አወጣጡና፣አለባበሱና አወራሩ እንደገመትኩት የአሁኑ ለውጥ ለየት ያለ መሆኑ ገብቶኛል። በአጭሩ ጎረቤቴን ደልቶታል በቅርብ አንድ ቀን እንደ ድንገት ተገናኘንና ሲያየኝ በደስታ ፈነደቀ ።አንድ ሊያሽሟጥጥ የፈለገው ነገር እንዳለ ወዲያው ገባኝ። ያችን የለበጣ ፈገግታውን አሳይቶኝ ፡ -

"እንዴት ነው ፖለቲካ ?"ብሎ ጠየቀኝ ።

"አንተ እንደተውከው" ብዬ መለስኩለት ።

"የአንድነት ኃይሉን ምን ነካው ተበታተነ ?" ብሎ ጀመረኝ ።

"ዘረኞች በዝተው ይሆናላ!"አልኩት ።

"አትቀልድ ያልኩህ ትክክል እንደነበር አስታውስ" አለኝ ።ከዚህ በፊት ስለትግልና ስለ ንግድ አንድነትና ልዩነት ያለኝን ለማስታወስ በመሞከር።

" አገር ቤት ምን አዲስ ነገር አለ? ሙብራት በራሽን መሆኑ ቀረ እንዴ?" ብዬ ያ ሊያነሳብኝ የፈለገውን ስለ ሆዳሞች መፈክርን ውይይት የምሽነፍበትን መሸሻ ርዕስ ፈለግሁ ።

ከዛች ርዕስ መሸሼ ገባው መሰለኝ ከት ብሎ ስቆ "ካሁን ወዲያ ሻማን ለልደት ብቻ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀምበት ብሎ መለስ ያለውን አልሰማህም እንዴ?" ብሎ ሊያሾፍብኝ ሞከረ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲስ አበባ ሕዝብ ብቻ የሚመስለው መለስ የተናገረውን ቅርሻት፣ ቅርሻት የሚል ቀልድ ለመስማት አልፈለኩምና ከዚህ በላይ ቆይቼ ብዙ እንዳንመላለስ . . . . . .ለዛሬ እቸኩላለሁ ሌላ ቀን እንጫወታለን ብዬው እግረ መንገዴን በየወቅቱ እየተነሱ የደገፍናቸውና በእኛ ስም ሲነግዱ ቆይተው ለወያኔ ያደሩ መሪዎችን እያሰብኩና እየረገምኩ ፣ በዛውም የኃይል ሚዛኑ ያደላ ዕለት ጎረቤቴ የሚይዘውን አቋም እየገመትኩ ጉዞዬን ቀጠልኩ . . . . . .

. . . . . ጎረቤቴ ባለ ብዙ ጠባይና ባለ ብዙ ታሪክ ስለሆነ ሌላውን ሌላ ቀን ባጫውታችሁስ . . . . .

ሰለኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !

Beljig.ali@gmail.com